# የዐማራ ሕዝብ ግንቦት ሰባት ለተባለው የብልጣብልጦችና የፖለቲካ ነጋዴዎች ስብስብ ቦታ እንደሌለው በማያሻማ ሁኔታ አሳይቷል።

Muluken Tesfaw FB 2018/091/16

እንዲህ ነው!
****

የዐማራ ሕዝብ ግንቦት ሰባት ለተባለው የብልጣብልጦችና የፖለቲካ ነጋዴዎች ስብስብ ቦታ እንደሌለው በማያሻማ ሁኔታ አሳይቷል። በዴሞክራሲያዊ መንገድ "ዐማራን ያስበላችሁ የሕዝባችን ጠላቶች ናችሁ" ብሏቸዋል። ንጹሐን ልጆቻችን በእናንተ ምክንያት ጥፍራቸው ሲነቀልና ሰብአዊ ክብራቸው ሲደፈር ኖሯል፤ በቃችሁን አንፈልጋችሁም" ተብለዋል። አዎ ከዚህ በኋላ በዐማራ ሕዝብ ስም መነገድ አይቻልም!!!

የዚህ ቀጣፊ ድርጅት የፌስቡክ ግሪሳዎች እንደለመደባቸው "ሕዝቡ ድርጅታችንን ባሕር ዳር ላይ በደማቅ ሁኔታ ተቀበለው" እያሉ እንደለመደባቸው ሲቀጥፉ ታዝበናል። መልካም ነው። ቅጥፈታችሁን ራሱ የዐማራ ሕዝብ እየታዘበና በየቀኑ አንቅሮ እየተፋችሁ ነውና!!!

ይህ የፖለቲካ ነጋዴዎች ስብስብ ለደገፈው የአዲስ አበባ ወጣትም አልሆነ! ሁልጊዜም የፖለቲካ ትርፍ እናገኝበታለን ብለው ካሰቡ ሕዝብን ከመካድ የማይመለሱ ጉደኞች ናቸውና! መርህ ብሎ ነገር አልፈጠረባቸውም። የፖለቲካ ትርፍ የሚያስገኝ ከሆነ ከኦነግም፣ ከሕውሓትም፣ ከሻዕቢያም ... ጋር ለመሥራት ዝግጁ ናቸው። ሠርተዋልም።

ለዚህ ነው አንድም የዐማራ ልጅ ለእነዚህ ግፈኛ ጸረ-ዐማሮች ምንም ዓይነት ድጋፍ ማድረግ የለበትም የምንለው። እነዚህን የፖለቲካ ነጋዴዎች መደገፍ በእነሱ ምክንያት በሞቱ ወገኖቻችን ላይ መሳለቅ ነው፤ ከገዳዮቻችንና አስገዳዮቻችን ጋር አብሮ መብላት ነው። የወገኖቻችን አጥንት ይወጋናል፤ ደማቸው ይጮሃል!!! አይሆንም!!!! በምንም መልኩ አይደረግም!!!!

ዛሬ በደም-መልሹ የባሕር ዳር ሕዝብ የተሠራው ሥራ በሁሉም የዐማራ ከተሞች ይደገማል!!! ገዳዮቻችንና አስገዳዮቻችን እንደግፍም!!!!



